# አገርን መውደድ አገርን ማልማት ነው
## ክፍል አንድ

በሲሳይ ሕሽ (Advocate for Ethiopia)
ቶሮንቶ ካናዳ

ሰሞኑን ከወደ ካናዳ የተናፈሰው ከእውነተኛ ተግባሩ በላይ ያበጠ፣ በማስመሰል የተቀለለና በህልም ተስፋ የታጀለ የጫሂዎች ፕሮፖጋንዳ በጥቂት ድረገፆች ላይ ተሰራጭቶ አየሁትና በመጀመሪያ የስርወ ነገሩ መናኛነት፣ የባለሴራዎቹ ብክነትና የውነተኛ ገፅታቸው ዋጋ ቢስነት በማጤን ሁኔታውን "አይጥ በራሷ አቅም በቀሰም ትታገም" የሚለው የዘመዶቼን ምሳሌ አስታውሼ በመሽታ ቤት ኮማሪቶች ዘዬ ኡኡቴ! ብዬ ተሳልቄበት ሳላበቃ የአቤት ባዮቹ ጠሊቅ "ራዕይ" ምን እንደሆነ ለመረዳት ያስችለኝ ዘንድ www.humanrightsethiopia.com የሚለውን የሰዎቹ ድረገፅ የተለያዩ አምዶችን (ገፆችን) እየከፈትኩ ማንበብ ጀመርኩ።

ድርጊቴ ታዲያ እራሴን መልሶ አሳቀኝ። የዛሬ ስምንት አመት ገደማ ጥቂት እራሴን አጎሳቁዬና አድክሜ ለነፋስና ለብርድ በመጋለጤ ሳቢያ የመተንፈሻ አካሌ ተቆጥቶ ባግባቡ መተንፈስ አቅቶኝ ጉሮሮዬ እርስ በርሱ እንሚፋጭ ፕላስቲክ እያፏጨብኝ መፍትሄ ፍለጋ ሃኪም ዘንዳ ሄድኩኝ። መጀመሪያ ያየቺኝ ነርስ ታሪኬን ነግሬያትና በማዳመጫ መርምራኝ ካለማንገራገር በሽታዬ *አስም መሆኑን* ተቀብላ ዶክተሩን *"አስም ያፈነው ህመምተኛ አለና ቅድሚያ ብንሰጠውስ?"* ብላ ጠይቃ ቅድሚያ ተሰጥቶኝ ከገባሁ በሁዋላ እንደወትሮው ያጠረኝን አየር የሚያስተካክል እርዳታ መበስጠት ፋንታ ዶክተሩ የሽንት፣ የደም፣ ያይነ ምድር፣ የራጂና የአልትራ ሳውንድ ምርመራ አዞ ውጤት ይገኙ ስመለስ ህመሜ ምን እንደሆነ እንደሚያውቅና መድሃኒት እንደሚሰጠኝ ነግሮ ደረቴ ሲር ሲር እያለ ወደ ላቦራቶሪና ራጂ ክፍል ሄድኩኝ።

ከሰዓት በሁዋላ ህመሙ እየባሰብኝ የቆዳዬ ቀለም እስኪቀየር ድረስ ስጨነቅ ውዬ ከነውጤቴ ዶክተሩ ምርመራ ክፍል ውስጥ ስገባ ውጤቱን ለይስሙላ መልከት ብሎ *"ያመመህ አስም ነው"* ብሎ የማውቀውንና የነገርኩትን ህመም ደግሞ ሲነግረኝ *"እርግጠኛ ነህ ዶክተር፣ ይሄ ነገር አሜባ አይደለም?"* ስለው የተነቃቃን ዓይነት ሾርኔያዊ ሳቅ ስቆ *"ለጊዜው እንግዲህ ያመመህ አስም ነው።"* ብሎ ቢያበቃስ ቀጠለና ደግሞ "አሜባው *በሌላ ጊዜና ምርመራ ሊገኝብህ ይችል ይሆናል"* ብሎ አናደደኝ።

የዚህ *የኢትዮጵያ ፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴ በካናዳ* ተብዬ ስዕሉ በሌሉ ሰዎች ጥላ የተሞላ የጥቂት ሰዎች ስብስብ ህመምም ገና ለህልመኛ ዓላማቸው ይረዳ እንደሆን በማሰብ ባሰራጩት ፕሮፖጋንዳዊ ፅሁፍ ርዕስ ብቻ ማወቅ ሲቻል በግልፅ የተጠናወታቸውን የጭፍን ጥላቻ ህመም ለመመርመር ያንን ሁሉ ገፅ ሳገላብጥ መዋሌ ተግባሬን ከዚያ ከሰዎች ስቃይ ከሚያተርፈው ሃኪም ጋር የተመሳሰለ ሆኖ ተሰማኝ። ይሁን እንጂ የዓላማው አልተገናኝቶነት ስለተገለፀልኝ የበለጠ ግንዛቤ ማግኘቴ *"ክፍርደገምድልነት"* ይታደገኛል በሚል እምነት ድርጊቴን አሞገስኩት።

አሃዱ፦ እነዚህ ሰዎች አገራቸው ኢትዮጵያን በውነት ይወዷታል ወይ? በሚል ጥያቄ ስጀምር መልሱን መስጠትም ሆነ መሻት አልፈለግኩም። ይልቅስ መውደድና ማፍቀር የተባሉት ተመሳሳይነት ያላቸው ቃላት የመዝገበ ቃላትና ማህበራዊ ፍቺያቸው ማወቁ የበለጠ ይረዳል ብዬ አሰብኩ። ፍቅር ካለ ምንም ቅድመ ሁኔታ ለተፈቀረው ወገን የሚቸር ከቁሳዊና ዓለማዊ መለኪያ ባያሌው የራቀና ሰጪውም ሆነ ተቀባዩ የሚረካበትና "የሚባረክበት" ረቂቅ ህሊናዊ ክስተት ነው።

የወደደና ያፈቀረ ሰው ለመስዋእትነቱ ዋጋ እንዲከፈለው አስቦ አይሰራም። አገሩን በእውነት የሚወድ ደግሞ ከጥቃት ይጠብቃታል፤ ያለማታል። እውስጧ ችግር ቢኖርም እንኳ እናቱ ነችና ገመናዋን ምንም ለማያደርጉላት ሰዎችና ለታሪካዊ ጠላቶቿ አሳልፎ እየሰጠ እንድትዋረድ አያደርግም። ምክንያቱም እናቱን በማንኳሰስና በማዋረድ የትልቅነትን ቦታ ያገኘ የለምና ነው።

ልጆቿ ለክፍለ ዘመናት ጠፍሮ ከያዛቸው ድህነት ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ለመገላገልና ያገራችንን ስዕል ለመለወጥ ካለመታከት ደፋ ቀና በሚሉበት ባሁኑ ጊዜ በዓለም ኢኮኖሚያቸው በፍጥነት ከሚያሳድጉት አምስት አገሮች አንዷ ኢትዮጵያ መሆኗ በምዕራባውያን እንደበት ሳይቀር በተገለፀበት ባሁኑ ጊዜ ዕድገቷ እንዲፋጠን በመተባበር ፋንታ ለሷ የሚሰጠውን እርዳታ ለማሰናከልና ቢችሉ ወደነበረችበት የጨለማ ዘመን እንድትመለስ የሚያደርግ አፍራሽ ፕሮፖጋንዳ ማሰራጨት መቼም በየትኛውም መለኪያ ቢለካም ጠላትነት እንጂ ወዳጅነት ሊሆን አይችልም።

ከነችግርዋ ያገራችንን ቀጣይ ህልውና እውን ለማድረግ የማይፈልጉና ለውርደቷ የሚተጉት ሁሉ ህዝቧ በንቃት እንደሚከታተላቸውና ሁልጊዜ በጠላት አሽከርነትና በምንደኝነት የሚነሱትን ሁሉ በተለመደው መንገድ እንደሚቀጣቸው የታወቀ ነው።

ክሌቱ፦ የአመለካከት ልዩነት ውበትና ለዕድገት መወጣጫ መሰላል አድርጎ ከመቀበል ይልቅ ያስተሳሰብ መራራቅ ለዕልቂትና ለግድያ ምክንያት እየሆነ ለየት ያለ ሃሳብ የያዘውን ለማሳመንና ለማስተማር ጊዜ ሳይሰጡ የሚረሽኑት ደርጎችና በወቅቱ ለዚህ ውድቀት እርሾ ሆነው ያገለገሉት ኢህአፓዎች በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ ያደረሱት በደል እንኳንስ ባለታሪኩ ቀጣዩ ትውልድም ቢሆን ይቅር የማይለው በደል ነው። እጅጉን የሚያስገርመው ደግሞ ይህ የካናዳው ቡድንም የዚሁ የኢህአፓ አባካቶ መሆኑ ነው።

ኢህአፓ የኢትዮጵያን ዕድገትና ብልፅግና ለማምጣት ሳይሆን ህሊናቸውን በትምክህት ሻሽ ሸፍነው ከምሁርነት ባሻገር የብፁእነትን ቦታ በተመኙ፣ ንኡስ ከበርቴነት ያሳበጠው መንፈሳቸው ከሰፊው የኢትዮጵያ ገበሬ ጎን ቆመው ለተቀደሰ ለውጥ መስራት ሲያቅታቸው በወቅቱ ከገጠር ወደ ከተማ የሚለውን ሳይንሳዊና ተግባራዊ የትግል ስልት አንፈልግም ብለው በየሰፈሩ ባቋቋሟቸው ስኳዶች አማካኝነት ተቃዋሚ አልያም ሊያደናቅፈን ይችላል ብለው ያሰቡትንና የጠረጠሩትን ሁሉ በመቆንፀል ከተሞቻችንን በንፁሃን ደም ያጨቀየው ነጭ ሽብርን

ያካሄዱትና የመሩት፣ ለቀይ ሽብር መፈጠር ቀንደኛ ምክንያቶቹ ኢህአፓዎች ከተቀበሩበት ጉድጓድ ተመልሰው እንዲመጡ የሚያልም ካለ እሱ የህዝባችን ጠላት ነው። በወቅቱ ቀንደኞቹ የኢህአሰ መሪዎች *"ደርግን በትጥቅ ትግል ከማቸነፍ ራስ ዳሽንን በገመድ መጎተት ይቀላል"* ብለው ከከተማ ወደ ከተማ የሚለው አግጣጫ ሲከሽፍ ከትግል ሜዳ ወደ ስደት ያመሩት ሳይሆኑ የሰፊው ህዝብ ታሪክ ሰሪነትን ያልተጠራጠሩት የህዝብ ልጆች ያኔ ከኢህአፓ አፈንጋጮች ጋር ወደ ውጭ ሳይፈረጥጡ ከሌሎች የነፃነት ታጋዮች ጋር በመሰለፍ መደባዊ ባህሪያቸው የሚፈቅደውን እምነት ይዘው ከድሃ ገበሬው ጋር አፈር መስለው አፈር ልሰው የመጡትና አሁንም ኑሮውን ኑሮአችን ብለው ለለውጥ የሚተጉት ኢህዴኖች (አብዛኛዎቹ ያሁኖቹ ብአዴኖች) ናቸው በፖለቲካ አመንዝራነት ከተቃጠለው ቡድን እንደ ወርቅ ነጥረው የወጡት። ስለነሱ ቢናገሩ ነው ድሃው የኢትዮጵያ ገበሬ የሚሰማቸውና ከጎናቸው የሚቆምላቸው።

ሰለስቱ፡- ሌላኛው የዚሁ ቡድን አስገራሚ አስተሳሰብ ደግሞ ኢትዮጵያ ያወጣችው ሽብርተኝነት የሚቃወም ህግ መውጣት አልነበረበትም ማለቱና ህጉን ያፀደቀችው በዚሁ በኩል የፖለቲካ ተቃዋሚዎችን ማሰር ስለምትፈልግ ነው ብሎ ማሰቡ ነው።

በመጀመሪያ የአሸባሪነትን ተግባር ለመፈፀም የግድ የጅሃድ ወታደር መሆን፣ አፍጋኒስታን ሄዶ ወታደራዊ ስልጠና መቀበል አልያም የአልቃይዳ መዋቅር ውስጥ መታቀፍን አይጠይቅም። ያንዲት ሉአላዊት ሃገር ሁለንተናና የህዝቧን ሰላም ለማወክ፣ በሁከቱ አማካኝነት በሚፈጠረው እልቂት በኩል በህፃናት አስከሬን ላይ እየተረማመደ ስልጣን ላይ ለመቆናጠጥ አስቦ ለህገ ወጥ ተግባር የሚደራጅ፣ የሚያደራጅና በማንኛውም መንገድ ድርጊቱን የደገፈ ሁሉ አሸባሪ ነው።

የዩናይትድ ስቴትስ *ፓትርዮቲክ አክት* ተረቆና በፓርላማ ፀድቆ ሲወጣም በመሰረቱ ከአሸባሪዎች ወገን ተመሳሳይ ተቃውሞ አጋጥሞት ነበር። ህጉ ንፁህና ሰላማዊ የሆኑ እስላም አሜሪካውያንን አደጋ ላይ ይጥላል የሚል ስጋትና ብዥታ እንዲፈጠር ሞክረው ነበር። ይሁን እንጂ ህልም ተፈርቶ ሳይተኛ አይታደርም እንደሚባለው ሁሉ ህጉ ህግ ሆኖ ከመውጣት ያገደው ሃይል አልነበረም።

በተመሳሳይ የካናዳው ፀረ አሸባሪነት ህግም እንደዚሁ በአሸባሪዎችና በደጋፊዎቻቸው በኩል የሰላ ሂስ ተሰንዝሮበት ነበር። እነዚህ የባህር ማዶ ተቃዋሚዎች ካገራችን የሚለዩት ግን የኛዎቹ እራሳቸውን የፖለቲካ ተቃዋሚ ነን ብለው ያምናሉ እነዛ ግን በቀጥታ የሚቃወሙትን ይናገራሉ።

በዚህ ዓለማችን በአክራሪ "ሃይማኖተኞች"ና ፅንፈኛ አስተሳሰብ ባላቸው አደገኛ ሃይሎች በታወከችበት ዘመን የፀረ አሸባሪነት ህግ ያፀደቀችው ኢትዮጵያ ብቻ አይደለችም። በርካታ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ከጉዳዩ ጋር ተናክኦት ያላቸው መንግስታትም የዜጎቻቸውን ደህንነት ለመጠበቅ ሲሉ ህጉን አፅድቀውታል። እነዚህ የካናዳ ተቃዋሚ ነን ባዮች ግን አገራችንን ምንጊዜም እንደ ሉአላዊት ሃገር የመቀበል ችግር ያለባቸው ይመስሉኛል፤ አልያም ደግሞ

የኢትዮጵያ ምሉእነት እነሱና ጋሻጃግሬዎቻቸው ስልጣን ላይ ካልወጡ ሊረጋገጥ የማይችል ይመስላቸዋል፤ የሚል እምነት አለኝ።

ይኸው *የፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴ በካናዳ* የሚባለው ድርጅት ከሚሞግትላቸው ድርጅቶች አንዱ ኦነግን እንውሰድ። ኦነግ የኦሮሞ ህዝብ የነፃነት ጥያቄ አንግቦ ቢነሳም የህዝቦች ነፃነት ተረጋገጠ በሚባልበት ዘመን በሰላማዊ መንገድ እታገላለሁ ብሎ ወደ አራት ኪሎ መጥቶ ከአገራችን ተወካዮች ጋር በጊዚያዊ መንግስቱ ውስጥ ስልጣን ከተከፋፈለ በሁዋላ ያ ለነፃነት ታገልኩ ያለው ግንባር ደርግ ከፈፀመው በማይተናነስ መልኩ ራሳቸውን መከላከል በማይችሉ ሰላማዊ ዜጎች ላይ ግፍና ሰቆቃ ሲያደርስ *"ከድርጊትህ ታቀብ"* ተባለ። ትችቱና ቀጣዩ እርምጃ ያሰጋው ኦነግ የክብር መድረኩን ጥሎ አጋሚዶነትን እንደመረጠና የሽብር ተግባሩን በከፋ ሁኔታ እንደቀጠለበት ይታወቃል።

ይህ በኢትዮጵያዊነታቸው የሚኮሩ ዜጎቻችንና ለክፍለ ዘመናት ለሉአላዊነቷ አኩል መስዋእትነት የከፈሉትን ህዝቦች ወኪል ነኝ ብሎ ያስብ የነበረውና አገራችንን ካለም ካርታ ለማስወገድ ከተነሱት ከሻዕቢያና ከአልሻባብ ጋር ግንባር እየፈጠረ በህዝባችን ላይ በደል የሚያደርሰው ቡድንን በሰውነት ሚዛን ላይ አስቀምጦ የሚሞግት ሰው እራሱ ከገዛ ህሊናው ጋር እንጂ ከኢትዮጵያውያን ጋር እንዲታረቅ አልመከረውም።

በየትኛውም መለኪያ ቢለካም ኦነግ በበደኖና በሌሎች የአገራችን አከባቢዎች በህፃናት፣ በሴቶችና ቤት በዋሉ ደካሞች ላይ ያደረሰው አሰቃቂ ግፍ አሸባሪነት ነው። በህፃናትና በነፍሰጡሮች አስከሬን ላይ የሚፎክርም ደግሞ የአሸባሪነት እንጂ የአርበኝነትን ማዕረግ መስጠት እጅግ አሳዛኝና ቆሻሻ አስተሳሰብ ነው። ይህንን አመለካከት የሚያራምድ ሰው በራሱ ጊዜና ሁኔታ ቢፈቅድለት ተመሳሳይ ድርጊት ከመፈፀም ወደሁዋላ እንደማይል ለመናገር የስነ አእምሮ ሊቅ መሆንን አይጠይቅም።

ምናልባትም በዚሁ ትንታኔ በኩል ይመጡብናል የሚል ፍራቻ ሰንቀው ዓለም በሙሉ እያፀደቀው ያለውን ፀረ ሽብርተኝነት ህግ ለምን ድሃዋ ኢትዮጵያ አፀደቀችው ብለው የሚሰጉ ካሉ እነሱ እራሳቸውን ይፈትሹ እንጂ አገራችን ግን ሀጉ ያስፈልጋታል። እነዛ የኢትዮጵያን ህዝብ ለማሸበርና ሰላሙን ለማደፍረስ ሎጂስቲክስና አመራር ከሚሰጡት የአልሻባብና የሻዕቢያ መሪዎች ጋር የሚገናኙትና ከጠላቶቻችን ቡራኬ የሚቀበሉት በህጉ መፅደቅ ይስጉ እንጂ ኢትዮጵያ ማንንም ለማሰር ፍላጎት ካላት ይህንን ህግ ማፅደቅ አያስፈልጋትም ነበር። ምክንያቱም ከገደብ ጀምሮ እስከ ሞት ፍርድ ማስወሰን የሚያስችል ከ1949ዓ.ም ጀምሮ ሲሰራበት የቆየ የወንጀለኛ መቅጫ ህግ አላት። ከዚያ በፊት ግን ለዚሁ የካናዳ ቡድን አንድ ከሚለው ጋር የሚጋጭ አባባሉን እንዲያብራራልኝ እፈልጋለሁ። ደጋግመው እንደሚሉት አሁን በአገራችን በስልጣን ላይ ያለው መንግስት ካለምንም ህግ ሰላማዊ ተቃዋሚዎችን ያስራል ካሉ ስለ ህግ መፅደቅ እንዴት ተጨነቁ? እንዳሉት በህግ የማይሰራበት አገር ከሆነ ህግ ተረቀቀ፣ ፀደቀ፣ ተሻረ ምን የሚፈይደው ነገር አለ?

እጅጉን ያሳዘነኝ ግን የኢትዮጵያን ነባራዊ ሁኔታ ሳያውቁና የህዝቡን ስነልቦናዊ ዘይቤ የደረሰበትን እርከን ሳይገነዘቡ እኛ እናውቅልሃለን የሚሉ ሰዎች ባለው መንግስት ላይ ያላቸውን ጥላቻ ለማሳየት የሚጠቀሙት ዘዴ መንግስት ላይ የፖለቲካ ጫና እንዲፈጠር መጠየቅ ሳይሆን ለኢትዮጵያ እርዳታ እንዳይለገስ ቃል የተገባ ካለም እንዲደናቀፍ በየፓርላማው ደጃፍ ማላዘን ነው። ለህዝብ ጠቀሜታ ያላቸው ፕሮጀክቶች በገንዘብ እጥረት ምክንያት ሽባ እንዲሆኑ ማድረግ በስልጣን ላይ ያለውን መንግስት እንዲገረሰስ ይረዳናል የሚል መላምት ይዘው ላይ ታች ቢኳትኑም በተግባር ግን ቅንጣትም ታህል ውጤት ማግኘት አይችሉም። ምክንያቱም አጋዥ መንግስታት እንዲሁ በተባራሪ ወሬ ከፍተኛ ጠቀሜታ ያላቸውን ተግባራት እንዲቋረጡ አያደርጉም። ይልቅስ ኢትዮጵያ ውስጥ ባሉ ኤምባሲዎቻቸውና ቆንስላዎቻቸው የጉዳዩ እውነተኝነት ያጣራሉ። እነዚህ በጭፍን ጥላቻ የሚነዱት ሰዎች እንደ ካናዳና አሜሪካ ያሉ የበለፀጉ ሃገሮች በኢትዮጵያ ውስጥ ባለሙሉ ስልጣን አምባሳደሮች፣ ዲፕሎማቶችና የፖለቲካና ወታደራዊ ጉዳይ የሚከታተሉትን ጨምሮ የተለያዩ አታሼዎች እንዳሏቸው እንኳ በውል የሚያውቁ አይመስለኝም።

ከላይ ከገለፅኩት አሰራር ውጭ ማንም ተነስቶ አካኪ ዘራፍ ባለ ቁጥር ብድግ ብሎ እርዳታ የሚያቋርጥና ማዕቀብ የሚጥል መንግስት የለም። እንደዛ ባይሆን ኖሮ በአውሮፓና በሰሜን አሜሪካ በተለያዩ ወቅቶች የተደረጉ ሰልፎችና ጩኸቶች ውጤት ጯኺዎቹ እንደሚፈልጉት ሆኖ ይታይ ነበር።

አርባዕቱ፦ በአንድ ወቅት እንኳንስ ኢትዮጵያውያን አፍሪካውያን የሚኮሩበት አየር መንገዳችን ወደ ካናዳ እንዲበርና ካናዳ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልድ ኢትዮጵያውያን ካገራቸው ጋር ያላቸው ትስስር በማጠናከር በኩል ጠቀሜታ ይኖረዋል ሲባል በከፍተኛ ቁጣ የተቃወሙት ሰዎች በምን መለኪያ ለኢትዮጵያ ህዝብ አሳቢ ሊሆኑ ይችላሉ? የኢትዮጵያ ምርት የሆኑና ካለው መንግስት ጋር ምንም ዓይነት ፖለቲካዊ ዝምድና የሌላቸው አምቦ ውሃና ሌሎች መጠጦች በየትኛውም የአበሻ ምግብ ቤት እንዳይሸጥ የጣሩትና ያልተሳካላቸው ሰዎች የኢትዮጵያና የኢትዮጵያዊነት ጠላቶች እንጂ በምን መለኪያ ወዳጆች ሊሆኑ ይችላሉ?

ምዕራባውያን ጋዜጠኞችና የታሪካዊ ጠላቶቻችን ምንደኞች እንደሚገልፁት የኢትዮጵያችን ገፅታ ሁሌ ብልሹና አሳፋሪ ሆኖ እንዲታይ ስለሚፈልጉ ነው በተቃውሞ ሽፋን ስዕሏን የሚያጎሉ ተግባራት እንዳይታዩ አጥብቀው የሚታገሉት።

የህዝቧ ኩራት የሆነው አየር መንገድ በካናዳ ሰማይ ላይ ቢበር አገራችን ውስጥ መኪና እንኳ እንደማይነዳ አድርገው የሚያናፍሱት የሃሰት ፕሮፖጋንዳ ጥያቄ ውስጥ ይገባና ያጋልጠናል በሚል ስጋት እንጂ አየር መንገዳችን በካናዳ በረረም አልበረረም በስልጣን ላይ ያለው መንግስት የህዝብ ጠላት ከሆነ ከውድቀት አይታደገውም። ደርግ የወደቀው ፀረ ህዝብና ወንጀለኛ ስለሆነ በጀግኖች ክንድ ተቀጥቅጦ እንጂ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ወደ ምዕራባዊ ንፍቀ ክበብ ባለመብረሩ አለያም የአምቦ ውሃና የቢራ ሽያጭ ስላላገኘ አይደለም። እነሱ ተበዳይ አስመስለው የሚያቀርቡት ኢህአፓ ብትንትኑ የወጣው በያዘው ዓላማ መክለስና በአስተሳሰብ

ንቅዘት እንጂ ካገር ውስጥም ሆነ ከውጭ ሃገር በተሰነዘረበት ተቃውሞ ብዛት አልነበረም።

አምስት፦ የአብዛኛዎቹ በውጭ ሃገር የሚንቀሳቀሱ ተቃዋሚ ነን ባዮች ዋነኛው ችግር ደግሞ ምርጫ በደረሰ ቁጥር ስለሃገራችን በቂ ኢንፎርሜሽን የሌላቸው በውጭ የሚኖሩ አገር ወዳድ ኢትዮጵያውያንን በማነሳሳት ገንዘባቸውን በዕርዳታ ስም ለመዝረፍ የሚንቀሳቀሱ መሆናቸው ነው። ይህ ካልሆነ ለምን የምርጫ ጊዜ ብቻ እየጠበቁ አካኪ ዘራፍ ይላሉ? ህዝባችን እነሱ ባስቀመጡት ደረጃ እየተበደለ ከሆነም ሰላማዊ ሰልፍ ብቻ አይፈታውምና ሰፊ ትግል እንድናካሂድ ሁልጊዜ ካለመታከት ሊቀሰቅሱን ይገባ ነበር። አምስት ዓመት እየጠበቁ እዬዬ ማለት ግን ዕርዳታ ከማሰባሰብና ኪስን ከማደለብ የዘለለ ጠቀሜታ አለው ብዬ ለማሰብም ሆነ ለማመን ፍላጎቱም ሆነ ቂልነቱ የለኝም።

ስድስት፦ ከላይ የዘረዘርኩት ከፍተኛ ምርምርና ዕውቀትን የማይጠይቀው ጥሬ ሃቅ የአንዳንድ አኩራፊዎችና የውጭ ተቃዋሚ ነን ባዮች አሻጥር ለማጋለጥ እንጂ በአገራችን ውስጥ ምንም ችግር የለም የሚል እንድምታ ያለው መልእክት ለማስተላለፍም አይደለም።

ከታሪካዊ አመጣጣችን አንፃር ሲታይ በርካታ በስነ ልቦናችን ውስጥ ስር የሰደዱ በቀላሉ ልንገላገላቸው የማንችላቸውና ለማሻሻል ብዙ ትግልና ልምምድ የሚጠይቁን ማህበራዊ ባህሪያት አሉን። እነሱ የሚፈጥሯቸው ተዛማጅ ችግሮችም እንደዚሁ በስልጣን ላይ ያለው መንግስት ባለስልጣናትም ዘንድ መከሰታቸው የግድ ነው፣ ባህሪያዊ በመሆኑ።

ለውጥ ለማምጣት በሚደረግ ውጣ ውረድ ውስጥ በርካታ ስህተቶችና የሰብአዊ መብት ጥሰቶች ሊከሰቱ እንደሚችሉ ጥርጣሬም የለኝም። ኢትዮጵያ የማይሳሳቱ ሳይሆኑ ከስህተታቸው የማይታረሙ አለያም ተሳሳትን የማይሉ መንግስታት እየገዟት ስለቆዩ ነበር መከራዋ የበዛው። አሁን ስልጣን ላይ ያለው መንግስት ካለፉት መንግስታት ከሚለይባቸው በርካታ መሰረታዊ ባህሪያት አንዱ ስህተቱን ፈትሾ ለቀጣይ እንዳይደገም መጣሩና ከሞላ ጎደል ተመሳሳይ ስህተቶች ደግመው እንዳይከሰቱ የሚያደርገው እንቅስቃሴ ነው።

እንዲህ ያለ አስተሳሰብና መርህ በራሱ ከነጎደሎውም ቢሆን ሊደገፍና ሊበረታታ ይገባዋል። አይ!...ይህም የኛ ቡራኬ እስካላገኘ ድረስ ስህተት ነው የሚሉ ወገኖች ካሉም አስተሳሰባቸው ግብዝነታቸውን ከማጉላት የዘለለ ፋይዳ የለውም።

ሰባት፦ ባገራችን በስልጣን ላይ ያለውና አገሪቱን በተጨባጭ ወደ አዲስ ምዕራፍ እየመራ ያለው መንግስትን የምወቅስበት ምክንያቶች ሞልተውኛል። አገሬን ላፍታም ቢሆን በህይወቱ የሚታደጋት አካልን ማረምም ሆነ መደገፍ አለብኝ ከሚል ፅኑ እምነት በመነሳትም ከነጎደሎው እደግፈዋለሁ። ይህ ማንም የማይፈቅድልኝ የግል እምነቴ ነው። በርካታ አገር ወዳድ ኢትዮጵያውያንም እየታየ ያለውን አንፃሂ ለውጥን በከፍተኛ ደስታና ሃላፊነት በተሞላበት መንገድ ይገልፁታል፣ ያጣጥሙታልም። ባንፃሩ ደግሞ ጥቂት ተሞክረው የወደቁት ስርዓታት

ርዝራዦችና በራሳቸው ምናብ እየተሳቡ ካለነሱ በጎ ፈቃድ ማንም ሰው ኢትዮጵያዊ መሆን እንኳ የሚችል የማይመስላቸው ግለሰቦች ያ በህዝብ ትግል ወደ መቃብር የወረደው ስርዓት ሊመለስ ይችላል በሚል ተስፋ ለእውነታው በማይመጥን የሃሳብ ፈረስ ተፈናጠው ወዳልታወቀ ግብ ሲጋልቡ ይታያሉ።

ስምንተኛ፦ ውጪ አገር ስለሚኖሩ ብቻ ከሌሎች ዜጎች የተለየ ተደማጭነት ያላቸው ለማስመሰል በተለያዩ ጊዜያት በሚያሰራጩት ፕሮፖጋንዳ አንዳንድ አገር ውስጥ ያሉት አኩራፊዎችን በሌለ ተስፈኝነት ሲያማልሏቸው ስመለከት አንዳንዴ እስቃለሁ። ለምሳሌ በካናዳ ማንም ሰው ማንኛውንም የፓርላማ አባል ለማናገር ከፈለገ ካለምንም ልዩነት ይስተናገዳል። የህዝብ ተወካይ አንዱ ስራ የሰዎችን ስሜት ማዳመጥን ያካትታልና ነው። የፓርላማ አባላቱ ሁሉንም ያዳምጡና አቤት ባዩን ሰው አቤቱታውን በበቂ ማስረጃ እንዲያስደግፈው ይነግሩታል። በመጀመሪያ ታዲያ ለራሳቸው ጉዳዩ ይመለከተኛል አይመለከተኝም ብለው የውይይቱን ርዕስ ይፈርጁታል።

ለዚህ ቡድን መነገር ካለበት የካናዳ መንግስት ግልፅ ፖሊሲ አንዱ ካናዳ በኢትዮጵያ የውስጥ ጉዳይ ላይ ጣልቃ የሚያስገባ ቅንጣት ታህል ስልጣን እንደሌላት ነው። ካናዳ ለሰብአዊ መብት ያላት ከበሬታ ጋር ተያይዞ ሊነሱ የሚችሉ መልካም እርምጃዎችን በማሰብ ዲፕሎማሲያዊ ሽምግልና ውስጥ ልግባ ካለች እንኳ የቀረበው ሪፖርት በሶስተኛና ታማኝ ወገን መረጋገጡና የስህተቱ አንፃራዊ ግዝፈትን መመዘን ያስፈልጋታል።

የካናዳ ፖለቲከኞች በጣም በሳሎች ከመሆናቸው የተነሳ ተቃዋሚ ነን ባዮች የኢትዮጵያ ድሃነት አጋንነው ቢተርኩላቸው ድህነታችን ካለው መንግስት ጋር ምንም ግንኙነት እንደሌለው ከሃያ ዓመታት በፊት በሲቢሲ ጋዜጠኛ ብራያን ስቴዋርት የተዘጋጀውን ዶክመንታሪ ፊልም ጠንቅቀው ያውቁታልና እንዲሁ በቁጣ ቃላትና በእርግማን ቋንቋ ሊሸወዱ አይችሉም፤ ይልቅስ ድህነት ቢኖርም ተስፋ ያለው ድህነት እንደሆነ ይነግሯቸዋል ብዬ አምናለሁ። የሚለቀሰውና የሚረገደው የመጨረሻዋን ህቅታ ጨርሶ በድን ለሆነ እንጂ ኢኮኖሚዋ ለበርካታ ተከታታይ ዓመታት በ10 እና በ11 ፐርሰንት እያደገ ላለችው ሃገር አይደለም። ፖለቲከኞቹ ይህንን አያውቁም ብሎ ጭፍን ጥላቻ ይዞ እርዳን የሚላቸው ሰው ሲመጣ ምን ዓይነት መልስ እንደሚሰጡትም የሚያውቁት ያውቁታል።

በቀጣይ ክፍል እስከምንገናኝ ደህና እንሰንብት!
ሲሳይ ሕሸ
ቶሮንቶ ካናዳ